# ትግላችን - ዜና

ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ሕብረት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board
P.O.Box 3198, 10364 Stockholm,3
SWEDEN


# የአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፳፩ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የፖለቲካ ውሳኔ


ጥቅምት 1977 ቅጽ 12 - ልዩ እትም

## ርዕሰ አንቀጽ

የ 24ኛውን ጠ/ጉባዔያችንን በምናካሂድበት ወቅት "የሠራተኛውን ፓርቲ"
ለመመሥረት በወታደሩ መንግሥትና ገበረአበሮች ከፍተኛ ዝግጅትና ቅስቀሳ ይካሄድ
ነበር ፡፡ እነዚህ ኃይሎች ይህን "የሠራተኛውን ፓርቲ" የሚያወጁበትን ቀን የራ
ባቸውን ታሪክ መፃፍያ ለማድረግ፣ "በዙ ተዓምር እንደሠሩና እንደፈጠሩ" ለመመፃደ
ቅ የተቻኮሉበት ጊዜ ነበር ፡፡

ጉባዔውና ማህበራችን ከዚህ ፓርቲ የሚጠብቀው አንዳችም አዲስ ነገር ባይኖ
ር ለኢትዮጵያ ህዝቦች የጽልመት ቀን፣በታሪካችን ውስጥ ደግሞ ትልቅ የታሪክ ጉድ
ፍ የጣለ መሆኑ ገልጽ ነው ፡፡ ሌላም፣ ህይወታቸውን በሙሉ ሰውተው በዝበዛንና
ጭቆናን ካለምንም ርህራሄ በመዋጋት ለእውነተኛ ነፃነት፣ የሰው መብት የሚከበርበት
ና ሰበአዊ ለሆነ ህበረተሰብ በታገሉት የታላቆቹ የወዝአደር መሪዎች ስም በኢትዮጵ
ያ ምድር ውስጥ በጥቂት ወረበሎችና ጋጠ ወጦች ስማቸው ሲጉደፍ የኢትዮጵያን ማርክ
ሲስቶች ሌኒኒስቶች ያበግናል፡፡ ይህንን ጉድፍ ለማስወገድ፣ የኢትዮጵያ ተራማጆች
ከባድ ተገባር እንደሚጠብቃቸው ፣ በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ትግሉ ከምንጊዜውም የበለ
ጠ አስቸጋሪ መሆኑን እንዲረዱት ያሻል ፡፡ ይህንን ስንል የዛሬውን የገዢ መደቦች
ለመቋቋም ችግር ይገጥማል ለማለት አይደለም ፡፡ የለም፡፡ በዛሬው አገዛዝና አስተ
ዳደር ገፍ የደረሰበትን፣ በሶሻሊዝም ስም ብዙ አሰቃቂ ድርጊት የወረደበትን ወገ
ናችንን ለማስረዳት፣ ትክክለኛውን ፈር ለማስያዝ የሚጠበቀን ተገባር ቀላል አለመሆኑ
ን ለማመልከት ነው ፡፡

ያም ሆነ ይህ ይህ "የሠራተኛው ፓርቲ " ታወጀ ፡፡ የዛሬው ገዦዎች "ብዙ
ብዙ ፃፉ፡፡ ሀገሪቱ፣ "በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ኑሮና በሌሎች መስኮች ወደፊት እንደተ
ራመደች" አይናቸውን በጨው አጥበው የኢትዮጵያን ህዝብና የዓለምን ህዝብ ለማሳመን ሞ
ከሩ ፡፡ እንደትልቅ "ድል" ብዙ የውጭ ሀገር መሪዎችና ዲፕሎማቶች ተጋበዙ፡፡ ለዝግጅ
ቱ ብቻ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደተደረገ፣ ከፍተኛ ሠርግና ምላሽ እንደ
ነበር የታወቀ ነው ፡፡ ነገር ግን ለዚህ ዝግጅት ይህንን ያህል ወጪ እየተደረገ፣ድ
ህነት በከተሞች፣ ረሃብና ድርቅ በሰሜን ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም የበለጠ ህዝባችንን
እያሰቃዩና እንደቀጠሉ እያረገፉ ነበር ፡፡ ነውም ፡፡ በይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ
ፓርቲውን ለመመሥረት ዝግጅቱ በሚጣደፍበት ወቅት ዕርዳታው ለተራበው ወገናችን እንዳይ
ደርስ ፣ " አሁን ሥራ ስለበዛብን ከፓርቲው ምሥረታ በኋላ ነው ዕርዳታውን ልናስተ
ባበር የምንችለው " እየተባሉ ከቢሮክራሲው መሥሪያ ቤቶች በረፍ ላይ የተመለሱት የ

ውጭ ሀገር ዕርዳታ ለጋሽ ድርጅት ሠራተኞች የሁኔታውን አሳዛኝነት በማወቅ በውጭ ሀገር ቴሌቪዥኖችና ሌሎች የዜና ማሠራጫዎች ተናገረዋል ::

ይሁንና ግን፣ ይህ ብዙ ዝግጅት የተደረገበት፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም 25 ገጽ የሚጠጋ ጽሁፍ በአብዮት አደባባይ ላይ ይዞ ወጥቶ ህዝብ ያስለቀበትና የተረከለት ፓርቲ ቀለም ባይደርቅ ፣ አሥራ አምስት ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ "ቢያንስ 60 ሺ ቶን እህል በየወሩ በዕርዳታ መልክ ካልመጣ በብዙ ሺ የሚቆጠር ህዝብ በረሃብ ይሞታል" የሚል የወታደሩ መንግሥት የሠጠውን የልመና ቃል በቢቢሲ በማን:: ይህንን ሁኔታ አስታኮ "ዕርዳታው በቢሮክራሲው አሻጥር የተነሳ በሚገባ ለተረበው ህዝብ አንደማይደርስ" ቢቢሲ አስታውቋል ::

እንግዲህ በውሳኔአችን ላይ ከፓርቲው ምሥረታ ቀደም ብለን እንዳባለነው፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከዚህ ፓርቲ የሚጠብቁት አንዳች ተአምር የለም :: በመሆኑም ትግላችን የበለጠ አጥፍ መሆን እንዳለበት፣ ከምንጊዜውም የበለጠ በተራማጆችና በብሔርና ብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች መሀከል መቀራረብን የሚጠይቅ መሆኑን መረዳት ያሻል:: ይህንን የታሪክ ሃላፊነት ለመቀበል የማንፈልግ ከሆነ፣ በሰበብ አስባቡ ለጋራ ግምባር የሚደረገውን ትግል የምናበናክል ከሆነ ወይንም ደግሞ በጊዜያዊ ዱላ እየታለልን የምንመረቃ ከሆነ በተጨባጭ ቢታይ እንደወታደሩ መንግሥት እኛም በታሪክ ፊት ከተጠያቂነት አናልፍም ::

ወ. ቦ



## <u>መግቢያ</u>

ኢትዮጵያ፣ አገራችን በአንዱ በኩል በአሳዛኝ በሌላ በኩል ለለውጥ በሚያበረታታና ተስፋ በሚሰጥ ሁኔታ ላይ ትገኛለች ::

በአገሪቱ ውስጥ የገባው ረሀብ ብዙ ሚሊዮን ሕዝባችንን መትቶታል::የዋጋ መወደዱ ጣሪያ ነክቷል :: በአገሪቱ ውስጥ የሸቀጣ ሸቀጦችና የእርሻ ምርት ውጤት እጥረት አለ :: በነጻ አውጪ ድርጅቶችና በወታደሩ መንግሥት መካከል የሚካሄዱት ጦርነቶች የብዙ ሰውን ሕይወት አነበሳ፣ አጸዋትና የአገሪቱ ሐብት በየቀኑ እየጠፉ ናቸው :: የአገሪቱ ሜዳዎች፣ ማሳዎችና ደኖች በምድሪቱ ላይ በሚወርዱ የቦንብና የመርዝ ጭስ እየጋዩ ናቸው :: ወደ አገራችን ከሩሲያ የሚገባው የጦር መሣሪያ ተዋጊ አውሮፕላኖች ፣ ሄሊኮፕተሮች፣ ታንኮች... አገሪቱን በስድስት ሚሊያርድ ብር ዕዳ ውስጥ ከቶታል ::

አገሪቱ የገባችበት የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ክሬዝ "በምሥራቅ ጥይትና በምዕራብ ዳቦ" ፈጽሞ ሊፈታ አልቻለም :: ሕዝባችን ይሰደዳል ፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ይታደናሉ :: የዲሞክራሲ መብቶች ታፍነዋል :: የሥራ አጥ ቁጥር ልክ አጥቷል :: ሕክምና ተጓድሎአል :: ትምህርት ቤት አይከፈትም :: መጓጓዣ መንገዶች አይጠገኑም :: ድልድዮች አይሠሩም :: ወንዞች አይገደቡም :: የአገሪቱ ምሁራን በባዕድ አገር ተከማችተዋል :: ይህ አገሪቱ የምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ ነው ::

ከሁሉም በላይ፣ የሚያሳዝነን ጥቂት መኮንኖች ሲደሰቱ በሺህ የሚቆጠሩ ሚሊሻዎች ተራ ወታደሮች በዱር በገደሉ ይወድቃሉ ::ጮማ ቢቆርጡ፣ ውስኪ ቢያፈሱ፣ ሠርግ ቢሠርጉና ቢደልቡ ተራው ሕዝብ የሚቆረጥመው ቆሎ የሚጠጣው ውኃ አጥቶ እየረገፈ ነው :: ለቅንጦት መኪና፣ ለአደባባይ ሠገነት ማሠሪያ፣ ለሠርቶ አደር ፓርቲ ማቢሠሪያ የአገሪቱ ገንዘቦች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ብሮች ቢያፈሱ ሕዝባችን ሜዳ ላይ እያደረ ነው ::

የአገራችን ሁኔታ ለለውጥ አመቺ በመሆኑ ደስ የሚልና ተስፋ የሚሰጥ ነው :: የተራበው ሕዝባችን ዳቦ ይላል በጦርነት የተንገፈገፈው ሰላም ይላል :: ፍትህና ፍርዱ የተጓደለበት ሕግና ስርዓት ይላል :: የመናገር የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣... የመተቸት፣ የመውቀስ፣ የመሰለፍ መብት ሕዝቡ ይጠይቃል :: የዲሞክራሲ መብት ሁሉም ይላሉ :: ብሔሮችናብሔረሰቦች እኩልነት፣ ነጻነት ይላሉ :: ሴቶች ወዝአደሮች ገበሬዎች ድርጅቶች እኩልነት ይላሉ :: የብሔራዊ ነጻነት ጩኸት ከፍ ብሎአል ::

ይህ መንግሥት ለአንዳም አንዳች መፍትሔ ለሕዝቡ ማቅረብ አይችልም ። የአገሪቱ ቀሬኝ እያበጠ፣ እየተረረመና እየከረረ ነው ። ቀሬኝው መፈንዳቱ፣ ይህም የወታደር መንግሥት መውደቁ የማይቀር ነው ። የአገራችን የኢትዮጵያ ሁኔታ እንደዚሁ ለለውጥ ተመቻችቶ ሲገኝ፣ ለዚህ ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ኃይሎች፣ ድርጅቶች በአንድ መድረክ ላይ በአለመሰብሰባቸው ሁኔታው አሳሳቢ ሆኖ አል ። በአገር ውስጥ የሕዝብ ወገኖች ተሰበጣጥረው ይገኛሉ ። የአገራችን የኢትዮጵያ ችግር በአገር አቀፍ ደረጃ መሠረታዊ መፍትሔ ካልተገኘለት አገሪቱ ከወደቀችበት ማጥ ፈጽሞ ልትወጣ አትችልም ።

ከ3.8.84 እስከ 6.8.84 በሙኒክ ከተማ የተሰበሰበው የአኢተማ ጠ/ ጉባኤ በኢትዮጵያ ጉዳያዊ ሁኔታ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ የሚከተለውን የፖለቲካ ውሳኔ አሳልፏል ።

<u>የብሔሮችናብሔረሰቦች እንቅስቃሴና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ሁኔታ፣</u>

የታሪክ ስሕተት ሆኖ ተረፍሞ የነበረው የመደብ ትግል ያን ያህል ቀዝቀዝ የብሔርናብሔረሰቦች ትግል ወደ መጀመሪያ ደረጃ ከተሸጋሸገ ጥቂት ዓመታት አልፈዋል ። የብሔሮች እስር ቤት ትባል የነበረችው አገራችን ከእስር ቤትነት አልፋ የጭቁን ብሔርናብሔረሰቦች ተወካዮችና ጭቁን ብሔረሰብናብሔሮች በስመ " ተገንጣይነትና " ጠባብነት " የሚረሸኑባት፣ ታፍነው ተወስደው መድረሻቸው የማይታወቅበት፣ የጥቂት ትምክህተኛ መኮንኖች መፈንጪ ሆናለች ብንል ማጋነን አይሆንብንም ።

ምንም እንኳ ጭፍጨፋና አፈናው ያን ያህል ቢበዛም የጭቁን ብሔርናብሔረሰቦች ተወካዮች መሣሪያ አንግተው በዱር በገደሉ በመሠማራት በዛሬ ጊዜ ከማናቸውም ጊዜ ይበልጥ ተጠናክረው በመታገል ላይ ናቸው ። ለዚሁም ነው ዛሬ ወታደራዊ መንግሥት ከመቸውም ይበልጥ ያለ የሌለ ኃይሉን ሰብስቦ በአራቱም ማዕዘን በጭቁን ብሔርናብሔረሰቦች ላይ የቦንብ መዓት የሚያወርድባቸው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የወታደሩ መንግሥት ለጭቁን ብሔርናብሔረሰቦች የቆመ ለመምሰል በጭቁን ብሔርናብሔረሰቦች ስም በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በነበረው



የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ምትክ አንድ " የብሔረሰቦች ኢንስቲትዩት " በአዋጁ አቋቁሟል ። የኢንስቲትዩቱ ዓላማና ይዘት ገልጾ ቢሆንም ከሞላ ጎደል ትምክህተኛ ምሁሮችን ያቀፈ ፀረ ጭቁን ብሔረሰቦች ተቋም ነው ። በመሆኑም፣ ማኅበራችን ይህንን የትምክህተኞች ተቋም አጥብቆ ይቃወማል ።

ማኅበራችን ለዘመናት ያህል ጠብቆ የኖረውን የብሔርናብሔረሰቦችን መብት እስከመገንጠል ድረስ ማወቁን አሁንም አያደበ፣ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ለመብታቸው የሚታገሉትንና በዛሬው ዕለት ፀረ የወታደሩ መንግሥት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ሳሉት ኢፒ ኤል ኤፍ ፣ ቲፒ ኤል ኤፍ ፣ ኦ ኤል ኤፍ ... እና ሌሎችም የጭቁን ብሔሮችና ብሔረሰብ ተጠሪ ታጋዮች ተገቢ የሆነ እርዳታ ለማበርከት ቃል ይገባል ።

<u>የገንዘብ ጥያቄ፣</u> የወቅቱን የኢትዮጵያን ሁኔታ በጥሞና ለተመለከተ በው ሁሉ የገንዘብ ጥያቄ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ አንገብጋቢ ነው ። በሕዝብ ስም ፀረ-ሕዝብ አገዛዝን ያስፋፋው፣የጥቂት ምርጥ መኮንኖች መንግሥት ከመቼውም ይበልጥ የውስጡ ያለውን ቀሬኝ አቻችሎ፣ያን ያህል ቀርጾ ቢስ እንዳልነበረ ሁሉ፣ዛሬ ከሞላ ጎደል አንድ ወጥ አዋሆን በመጠበት ባሁኑ ወቅት፣የተራማጅ ኃይሎች የጋራ ቷንቷ ያው ይመስል ተበታትነው የተናጠል ትግል ማካሄዳቸው የሚያሳዝን ነው ። በእርግጥ ከላይ እንደጠቀስነው በዛሬው ዕለት ከማንኛውም ሀገር አቀፍ ተራማጅ ድርጅት ይልቅ ተጠናክረው የሚገኙት የብሔርናብሔረሰቦች ነጻ አውጪ ግንባሮች ናቸው ። ሆኖም በነጻ አውጪ ግንባሮችና በሀገር አቀፍ ተራማጅ ድርጅቶች መሐል የመቀረረቡ ሁኔታ የአስፈላጊነቱን ያህል የሚያረካ አይደለም ። በእኛ እምነት በሁለቱም መሀከል የጋራ የሆነ ፀረ-የወታደሩ መንግሥት ትግል አለ ። ታዲያ ለምን የአንድነት ግንባር ሊመሠረት አልቻለም፣ የሚለውን ለመመለስ ጥቂት ቢያዳግትም፣ ጠቀሜነትና ቅንነት እንዲሁም መተማመን በመሐከላቸው ካለ የማይቀረረብበት ምክንያት ምንም አይታየንም ።

በዚህም እምነታችን መሠረት የተራማጆች መከፋፈል ለፀረ ሕዝቡ የወታደር መንግሥት ዕድሜ ማራዘም መሆኑን በመገንዘብ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የዛሬውን አገዛዝ በመቃወም የሚታገሉ የብሔርናብሔረሰቦች ነጻ አውጪ ግንባሮችና ሀገር አቀፍ ተራማጅ ድርጅቶች ያሳቸውን ጥቃቅን ልዩነቶች ለጊዜውም ቢሆን አቻችለው፣ "ጹኑ መንከራ ነኝና በእኔ ዙሪያ ተሰብሰቡ " የሚለውን አጉል ገብዝነት ትተው በቅንነት

ጉን ለጉን ሆነው የጋራ መርሐ-ግብር በመንደፍ በዛሬው አገዛዝና ግብረአበሮቹ ላይ የጋራ በትራቸውን እንዲሰነዝሩ ይህ ዝግጁ አብዮታዊና የሀገር ፍቅር የተሞላበትን ጥሪውን ያቀርብላቸዋል ። ማኅበራችን ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር ከሚታገሉት ጉን ሆኖ የአቅሙን ለማበርከት የገባውን ቃል ኪዳን እንደገና ያድሳል ።

## የረሐብና የስደት ጉዳይ

በዛሬው ዕለት በድርቅ ምክንያት ከተጎዱት 24 የአፍሪካ አገሮች ኢትዮጵያ አሰቃቂ ከሆነ ከፍተኛ ረሐብ ላይ የደረሰች መሆኑን በቅርቡ ዚምባብዌ ዋና ከተማ ሀራሬ ላይ ተደርጎ የነበረው የተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት ጠቁሟል ። በቅርብ ጊዜ ራሱ የኮሎኔል መንግሥቱ መንግሥትም እንዳመነው ከአምስት ሚሊዮን በላይ የሆነ ሕዝባችን በረሐብ አለንጋ በመገረፍ ላይ ነው ። በስድስት የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች በየቀኑ ከአምስቱ ሀጻን አንዱ በረሐብ ይሞታል ። በእርግጥ የዓለም የእርሻና ምግብ አዋቂዎች እንደጠቆሙት ሁሉ አፍሪካን ያጥለቀለቀው ረሐብ ጊዜያዊ መንስኤው የተፈጥሮ አደጋ ቢሆንም የሕዝብ ወገኖች ሥልጣን ላይ ቢሆኑ ኖሮ አደጋው በብዙ በቀነሰ ነበር ። ወታደራዊው መንግሥት የሀገሪቷን ሀብት ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሟጠጥ ለጦር መሣሪያ ግዥና ለግል ቅንጦት ዕቃዎች መግዣና እንዲሁም ለአሥረኛው " የአብዮት " በዓል ለማክበር የብዙ ሚሊዮን ብር ዝግጅት እንደሚያደርግ ለማንም ግልጽ ነው ።በሌላ በኩል አምራች የሆነው ኃይል ፣ ወጣቱን በሰበብ ባስባቡ በሚቀሰቅሰው የወሰን ግጭትና ፀረ ነጻ አውጪ ግንባሮች ጦርነት ላይ እያስማራ አገሪቱን ወጣት አልባ አድርጓታል ። ድርቅ በመታቸው አካባቢዎች የሚኖሩትም ወገኖቻችን ተኝቶ ከመሞት አገራቸው የቻለውን ያህል እየተጓዙ ወደ አቅራቢያቸው ወደ ሚገኙ አነስተኛ ከተማዎች በመጓዝ በልመናና ሥራ አጥነት የመሞቻ ቀናቸውን በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ በደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኃይላት ታፍነው ያለውድ በግድ "ከማይፈልጉት በመጠጊያቸው በረት" ውስጥ ይታጎራሉ ። የዚህም ውጤት፣ ደርግ በጉልበት የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦችን " በሰፈራ ፕሮግራም" ስም በማደበላለቅ ላይ ይገኛል ።በእኛ አስተያየት ይህ ዓይነቱ " የሰፈራ ፕሮግራም " መሠረታዊው የጭቁን ብሔርና ብሔረሰቦች መብት ባይታወቅ " አንድ ወጥ " የሆነች ኢትዮጵያን ለመመሥረት የሚደረገውን የደርግን ፕሮግራም ማኅበራችን አጥብቆ ያወግዛል ።



በእርግጥ ደርግ እንደ ኃይለ ሥላሴ "የኢትዮጵያን ሕዝብ መራብ አልደበቅም" "መራባቸውን ለዓለም ሕዝብ አስታውቃለሁ ፣ ከተጠያቂነት ዱኝአለሁ" ለማለት የሚሞክርም ይመስላል ። በውጭ አገርም ያሉት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በያሉበት አገር ረሐቡን አስመልክተው መግለጫ ከማውጣትም አልፈው ድርጅት/ግለሰቦች እርዳታ ሊለግሱ የሚችሉባቸው የባንክ አካውንት ከፍተዋል ። ውጤቱን እንደተከታተልነው ከሆነ በአንዳንድ አገሮች ወደ ተራበው ሕዝብ የሚሄድ ባይሆን ለኤምባሲው ውስጣዊ ጉዳዮች " ሥራ ማስኬጃ" መዋያቸውን ተገንዝበናል ።

ዛሬ በመላው ዓለም በተለያዩ ምክንያቶች አገራቸውን ጥለው ከሚሰደዱት በብዙ ሚሊዮን ከሚቆጠሩት ስደተኞች መሀከል ከ3 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ መሆኑን የዓለም ሕዝብ ያወቀው ጉዳይ ነው ።

ምንም ምንኳ ስደተኞች የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖራቸውም ብዙዎቹ ሀገራቸውን ጥለው የወጡበት ዋናው ምክንያት የወታደራዊው መንግሥት ፀረ-ሕዝብ አስተዳደር ነው ።

ማኅበራችን ለረሐብም ሆነ ለስደቱ ዘላቂ መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ከራሱ ጥቅም ይልቅ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ የሕዝብ የሆነ ዲሞክራሲያዊና ሕዝባዊ መንግሥት ሥልጣን ቢይዝ ብቻ ነው ብሎ ያምናል ። ፀረ-ሕዝቡን ደርግ ከሥልጣን አውርዶ ለበሳም የቆመ የሕዝብ መንግሥት ለማቋቋም በሚደረገው ትግል ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ። ለዚህም ተግባራዊ በሆኑ የእርዳታ መሰብሰብና ወታደራዊውን መንግሥት በማጋለጡ ዘመቻ ላይ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ተሳትፎ ያደርጋል ።

ማኅበራችን፣ የወታደሩ መንግሥት በጅቡቲ መንግሥት ሁለቱም የተባበሩት መንግሥታትን ውል በመጣስ የፖለቲካ ስደተኞች መብት በመገፋፍ የጅቡቲ መንግሥት በጅቡቲ የሚገኙትን ስደተኞች ለኢትዮጵያ ወታደር መንግሥት አሳልፎ የመስጠቷን እርምጃ ያወግዛል ።

ማኅበራችን በጅቡቲ ፣ በሱዳንና በሌላ አካባቢዎች መብታቸውን ለማስከበር ተደራጅተው ለሚገኙት የኢትዮጵያ ስደተኞች ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል ። ከእነዚህም ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመሥራት ሐሳብ ለመለዋወጥና አቅሙ በሚፈቅደው መሠረት ድርጅቶችን ለመርዳት ያለውን ሙሉ ፍላጎት በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል ።

## የኢኮኖሚ ሁኔታ

ካለፉት ወራት ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ የሚታተሙት ጋዜጣዎች በየጊዜው የሚያነሱት "ሀገሪቱ በኢኮኖሚ ዕድገትና በማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታዋ እንደተራመደች ነው":: በተለይ አዲስ ዘመን ጋዜጣ " አሥር ዓመት በትግልና በድል ጉዳና" በሚለው ርዕስ ስር: " ... የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በአብዮታዊው መንግሥትና በኢሠፓአኮ አመራር ባደረገው ትግል በፖለቲካ፣ በወታደራዊው፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች አያሌ ድሎችን ተጎናጽፏል :: " የሚሉ ቃላቶች በፍረው አናገኛለን :: / አዲስ ዘመን ሰኔ 29/1976 / ይህ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ሀገሪቱ ከምትገኝበት የኢኮኖሚ ውድቀት ጋር በፍጹም የሚመሳሰል አይደለም ::ይህ ኢትዮጵያ በረሐብ ምክንያት በዓለም ሕዝብ ፊት መጋለጧን ለመሸፈን የሚደረግ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ነው ::

አንኳን አንደ ኢትዮጵያ በአራቱ መዓዘን ጥይት በሚያፏጭበት፣ ብዙ ገንዘብና የሰው ሕይወት ለጦርነት በሚያልቅበት አገር ይቅርና " በሰላም የተደላደለ" መንግሥት የሰፈነባቸውና በቂ ሐብት አላቸው የሚባሉት ሌሎች የሶስተኛ ዓለም አገሮችም በኢኮኖሚ ሁኔታቸው እየተሻሻሉ የሚሄዱ አይደሉም :: የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ እንኳ ቢሆን ሰላምን አላገኘች ለኢኮኖሚ ዕድገቷና ለሕዝቡዋ የማኅበራዊ ኑሮ መሻሻል የሚበቃትን፣ ሕዝቡ በበሔራዊ ኢኮኖሚ ዘመቻ የሚያፈልበትን፣ ዕቅድ ወጥቶ ሀገሪቱ በኢኮኖሚ ግንባታ ወደፊት ስትገሰግስ የሚታይባት አገር አይደለችም ::

ሰላም ባልሰፈነበት፣ የኑሮ መመስቃቀል ባለበት፣ በፊውዳል ቡርዥዋ የመንግሥት መኪና ላይ የወታደሩ አምባገነን መንግሥት በተፈናጠጠበት ሀገር፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት በሌለበት፣ የሀገሪቱ ተወላጆች በሙሉ ልብ በግንባታ በማይሳተፉበት አንድ አገር በኢኮኖሚ በፍጹም ወደፊት ሊተራመድ አትችልም ::

የዚህ የኢኮኖሚ መድቀቅ ውጤት፣ የሕዝብ የመግዛት ኃይል በየጊዜው እየቀነሰ መሄዱና የዕቃዎችም በገበያ ላይ አለመገኘት ነው :: የአገሪቱ ኢንዱስትሪዎች



ከመጠን በላይ ያረጁ በመሆናቸውና በመለዋወጫና በጥሬ ሀብት ሙሉ በሙሉ የውጪ ጥገኛ በመሆናቸውና እንደምንም ለመንቀሳቀስ የሚችሉት ደግሞ የማምረት ችሎታቸው ከ30 ፐርሰንት በታች በመሆኑ የጠያቂውን ፍላጎት ለማሟላት አልቻሉም ::ሌሎች ለመንቀሳቀስ የማይችሉት ደግሞ ከሥራ ውጭ በመሆን ተቀጥሮ የሠራባቸው የነበረው ወዝአደር ካለምንም ካሣ የሥራ አጡን ሠፈር እንዲያጥለቀልቅ ተገዷል :: ይህ የምርት መቀነስ ዋጋዎችን ከፍ እንዲያደርግና ተጠቃሚውን ሕዝብ እንደሚጉዳው የታወቀ ነው :: በገበያዎች ላይ የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት እንደልብ ለመገኘት ባለመቻሉ ዛሬ የጥቁር ገበያ አራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሆኖአል :: ይህንን ከውጭ በየጠረፉ የሚመጣ ዕቃ ደግሞ ሊገዛና ሊጠቀም የሚችለው ገንዘብ ያለው ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው :: የዚህ የጥቁር ገበያ መስፋፋት የሀገሪቱ የኢኮኖሚና የገንዘብ የመግዛት ኃይል ላይ ከፍኛ እንዲቃወስ አድርጓል :: የአሜሪካ ዶላር የዚህ የጥቁር ገበያ መገበያያው ዋና ገንዘብ ሆኖአል ::በዚህም ምክንያት አንድ አሜሪካ ዶላር በአምስት የኢትዮጵያ ብርወይንም ከዚያ በላይ ይለወጣል ::ይህ የጥቁር ገበያ መስፋፋት አንደኛ ጎን ቢሆን ወደ ውጭ ደግሞ ቡና፣ ወርቅ፣ ቆዳ፣ የቀንድ ከብትና ሌሎች የሀገሪቱ ሐብቶች ጠረፍን እየተሻገሩ ወደ አካባቢ አገሮች በሽምቅ ሽያጭ ይጎርፋሉ :: በሌላ በኩል ለአገሪቱ ዕድገት የሚረዱ ኢንዱስትሪዎችና በተለይም ደግሞ ከእርሻ ሰብል ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችል ኢንዱስትሪዎች በአለመቋቋማቸው የተጠቃሚውን ሕዝብ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ፍላጎት ለማሟላት በፍጹም አልተቻለም :: ያሉት ያረጁትና ቀላል ምርት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች አሁንም እንደወትሮው በጥቂት ከተማዎች በተለይም ደግሞ በአዲስ አበባ ብቻ የተከማቹ ስለሆነ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የምርቶች ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም :: የኢንዱስትሪው፣ የቤትና የመንገድ ሥራ ከጠቅላላው የአገሪቱ ምርት 14 ፐርሰንት ብቻ አለው ::ይህ የሚያሳየው አገሪቱ አሁንም በኢንዱስትሪ ዕድገቷ ወደፊት ልትገፋ ያልቻለችና በየጊዜው ሥራ ፈላጊ ለሆነው ሳልተማረውና ትምሕርቱን አያጠናቀቀ ለሚወጣው ወጣት አዳዲስ የሥራ መስክ ለመክፈት ያልቻለች መሆኗን ነው :: የዚህ ውጤት ደግሞ በየጊዜው የሥራ አጡ ቁጥር ከፍ እያለ እንዲሄድና ወደሌሎች ጠቃሚ ወደ አልሆኑ ነገሮች እንዲሰማሩ ማድረግ ነው ::

በአገራችን የሥራ አጥ ቁጥር የማይመዘገብ ቢሆንም ቁጥሩ ከፍተኛ እንደሆነ በውጭ አገር እየታተሙ የሚወጡ የውጭ አገር ሪፖርቶች ያሳያሉ ::

የሀገሪቱ ሐብት በእርሻ ላይ የተመካ ቢሆንም፣ ለእርሻ ተገባር ለመዋል ከሚችለው ሰማንያ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ በግምት አስራ አምስት ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነው መሬት ብቻ ይታረሳል :: ይህም ደግሞ በጣም በተዘረከረከና ወደኋላ ቀር በሆነ መንገድ ነው የሚታረሰው :: ሀገሪቱ በዓመት ከአራት እስከ አምስት ሚሊዮን ቶን የሚጠጋ እህል ብቻ ስታመርት፣ ከአንድ ሚሊዮን ቶን በላይ እህል በየዓመቱ ከውጭ ለማስገባት ተገዳለች :: ይህ ሁኔታ፣ የምግብ እጥረትንና ውድነትን አስከትሏል :: በተጨማሪም፣ በአሁኑ ጊዜ በከተሞች ላይ ለእህል እጥረት ላለው ምክንያት በየጦር ሜዳው በከንቱ ደሙን ለሚያፈሰው በብዙ ሺህ ለሚቆጠር ወታደር የሚጋዘው እህል ከፍ በማለቱ ነው :: ይህ ክፍል ደግሞ ከኢኮኖሚ አንጻር ሲታይ አምራች ባለመሆኑ ከብዙኃኑ ተጠቃሚና አምራች አንጻር ሲታይ ድርሻው ከፍ ያለ ነው ::

ለሀገሪቱ ጠቅላላ ኢኮኖሚ መድቀቅ፣ ለዕቃዎች እጥረት፣ ለሥራ አጥ ቁጥር መብዛት ምክንያት፣ አገሪቱ ያለችበት የኢኮኖሚ ተቋም ብቻ ሳይሆን፣ በየቦታው ለሚካሄደው ጦርነት የሚፈሰው፣ ለጦር መሣሪያና ለጸጥታ የሚወጣው ዓመታዊ ወጪ ከሌሎች ለእርሻና ለኢንዱስትሪ ከሚወጣው ጋር ሲወዳደር የእጥፍ እጥፍ በመሆኑ ነው :: ለምሳሌ ለጦር መሣሪያና ለጸጥታ ተብሎ የሚወጣው ዓመታዊ ወጪ ከጠቅላላው ዓመታዊ ባጀት ውስጥ በአማካይ 35 ከመቶው ሲሆን፣ ለኢንዱስትሪና ለእርሻው 17 ከመቶ ብቻ ይወጣል :: ይህ ሁኔታ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ውጤት አስከትሏል :: የውጭ ንግድም ሁኔታ ስንመለከት፣ ሚዛኑ አሁንም የተዛባ ነው :: የ1982 ዓ.ም የንግድ ሚዛን ስንመለከት ወደ ውጭ ከተላከው ምርት የተገኘው ጠቅላላ ገቢ 835.5 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን፣ ወደ ውስጥ ለገባው የኢንዱስትሪና የእርሻ ምርት የወጣው ወጪ 1617.8 ሚሊዮን ዶላር ነው ::



በዚህ የንግድ ልውውጥ የከሰረችው ኪሣራ 782.3 ሚሊዮን ዶላር ነው ::

እንግዲህ አጠቃላይ ሁኔታውን ስንመለከት ኢኮኖሚው እየቆረቆዘና እየተዛባ የመጣ እንጂ በምንም ዓይነት የአሁኑ መንግሥት ሊያሳምነን እንደሚሞክረው፣ እያደገና እየተሻሻለ አይደለም ::

ይህ የ24ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ይህንን ሁሉ ከመረመረ በኋላ የወታደሩ አምባገነን መንግሥት በሥልጣን ላይ እስከአለ ድረስ በፍጹም የአገራችን ኢኮኖሚ እድገት የሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ሊሻሻል እንደማይችል በመገንዘብ፣

ሀ/ ይህ የወታደር መንግሥት ወድቆ በእሱ ምትክ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያድግበትንና የሕዝቡ ፍላጎት ሊያረካ የሚችል የዲሞክራቲክ መንግሥት እንዲመሠረት በሚደረገው ትግል ማኅበሩ የተቻለውን አስተዋጽኦ ያደርጋል ::

ለ/ ለጦር መሣሪያ ግዥ፣ ለፀጥታና ለቅንጦት ድግሶች የወታደሩ መንግሥት በከንቱ የሚያፈሰውን የሕዝባችንና የሀገሪቱን ሀብት በቅስቀሳና በፕሮፖጋንዳ እያነሳ በዓለም ሕዝብ ፊት ያጋልጠዋል ::

<u>ስለ ኢሠፓአኮ ከዚህ ውስጥ ይፈጠራል ስለሚባለው አሠፓ</u>

በትምክህተኝነት የተወጠረው፣ ሕዝባችንን ለጦርነት፣ ለስደት፣ ለረሐብ፣ ለብሔራዊ ውርደት የዳረገው የወታደራዊ አምባገነን መንግሥት አንዱን በአንዱ እየመታና እያስመታ ሌላውን እንዲያገበድዱለት በማድረግ፣ የሥልጣን ሞኖፖልን በእጁ ቁጥጥር ከአደረገ በኋላ ዛሬ " የኢትዮጵያን ሠራተኞች የሚወክል ፓርቲ" እፈጥራለሁ በማለት ጉድ ጉድ እያለ ነው :: የዚህ የፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን አመሠራረት፣ በሀገራችን ውስጥ ከፀረ-ዲሞክራሲ መንገስ፣ ከብሔራዊ ነጻነት መሸጥ፣ ከትምክህተኛ ጦርነት መስፋፋት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው :: በሬው የኢትዮጵያ ሕዝብና ነገር ቀደም ታጋዮች ስንት መስዋዕትነት የከፈሉበትን የሶሻሊዝምን አብዮታዊ ድሎች አንዱ በአንዱ እየቀለበሰና የወደፊት ኢትዮጵያን ገንቢ የሆኑትን ሀቀኛ ታጋዮች እየጠፈጠፈና እያስመታ ሙሉ በሙሉ የተደላደለ ሲመስለውና የልብ ልብ ሲሰማው በወዛደሩ፣

በገበሬውና በሀቀኛ ምሁር ስም ለመመጻደቅ፣ " የኢትዮጵያን ሠርቶ አደሮች የሚወክል ፓርቲ የሚያደራጅ ኮሚሽን " አቋቋሚአለሁ አለ ።

የዚህን ኮሚሽን መመሥረት የሚያበስር አዋጅ ለማውጣት የደርግ መሪዎች ደፋ ደፋ ቢሉ ቢያንስ ገና ያልተረጋጋውን ያለየለትን የጊዜውን አብዮታዊ ሁኔታ ለማብረድና " የኢትዮጵያ ሕዝብ የምትፈልገውን የሠራተኛ ፓርቲ ይኸውልህ ልናመጣልህ ነው " በሚል ሸሰታቸውን ለመንዛት ነበር ። ይሁንና ገን አዋጁ ቢወጣ የደርግ ሊቀመንበርና የዚህ አደራጅ ኮሚሽን አንድ ሰው መሆኑ ተገለጸ ። የጥቂትን ቡዶች የበላይነት ለማረጋገጥና የፀረ–ዴሞክራሲን አገዛዝ ለረጅም ጊዜ የሚያቆይ አዋጅ ሆነ ። በዚያን ጊዜ አዋጁን ለተመለከተው ከዚህ አደራጅ ኮሚሽን ሌላ ሌላ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ፓርቲዎች በሕግ የተከለከሉና የዚህ ኮሚሽን አጎብዳጅ የሆኑ ግለሰቦች ብቻ የሚሰገበዝበት ድርጅት ሆነ ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተቋቋመና ከዚህ ውስጥ የሚፈልቀው ፓርቲ ደግሞ በምንም ዓይነት የኢትዮጵያን ወዝአደሮች፣ ገበሬዎችና አብዮታዊ ምሁራንን የማይወክል መሆኑ ከአዋጁ በፊት ቀደም ብሎ የታወቀ ነበር ። አዋጅም ቢወጣ ያስመሰከረውም ይህንን ነው ።

የዚህ ኮሚሽን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትም ሆኑ መሪዎች አንድ የፀና የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ መስመር ያላቸው፣ ከረጅም ጊዜ የመስመር ትግል በኋላ ጊዜውን ጠብቀው በሐቀኝነት ላይ የተገነቡ ቡዶች አይደሉም ። በውስጡ የተቀፉትን ኃይሎች ስንመለከት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የከፍተኛውን ኅብረተሰብ ክፍል ይወክላሉ ከሚባሉትና ከመሐከለኛው የኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ነው ። ከፍተኛው የወታደር መኮንኖች፣ የድሮው የኃይለሥላሴ መንግሥት ቢሮክራሲና ቴክኖክራቶች የሥልጣን ፍርፋሪ ለማግኘት ያጎበደደው የነውስ ከበርቴ ምሁርና አድርባይ በዚህ ኮሚሽን ውስጥ በብዛት ይወከላሉ ። የእነዚህ ኃይሎች ሁሉ መደባዊ ምንም ይለያይ እንጂ አጠቃላይ ባሕሪያቸው ትምክህተኛነትና ፀረ–ዴሞክራሲነት እንዲሁም ደንፊነትና ጥሬዝ ነጠቅነት ነው ። ኮሚሽኑም ሆነ የኮሚሽኑ መሪዎች የሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለም አከተሳለሁ አያሉ የውሸት ፕሮፓጋንዳቸውን ቢነዙም፣ የሀገሪቱ ሁኔታ እንደሚያጋልጠው ከሆነና የሚከተሉትም ፖለቲካ እንደሚያሳየው በምንም ዓይነት ከሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም የሚያገናኘው አንዳችም ነገር እንደሌለ ነው ። ሌላው ቢቀር እንኳ ከተራ የከበርቴ ፓርቲ ደረጃ የሚደርስ አይደለም ። የዚህ አደራጅ ኮሚሽን ልዩ ርዕዮተ ዓለም ይኸኛው ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ባይቻልም፣ ከኮሚሽኑ መቀ



ቀርና ሀገሪቱ ካለችበት ኢኮኖሚ ሁኔታ አንጻር ሲመረመር አሁንም ቢሆን የፊውዳሉ መለዮች የሆኑት ርዕዮተ ዓለም ትምክህተኛነት ፣ ደንፊነት፣ ጉረኛነት ...ወዘተ የዚህ ኮሚሽን መለዮዎች ናቸው ።

በየቦታው ኢሠፓአኮን ለመመሥረት በሚደረገውና ዛሬም በኢሠፓ መመሥረቻ ወቅት በሚካሄደው ስብሰባ መረዳት የምንችለው ተራ አባላትም ሆነ በፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያብገነገኗቸውን ጥያቄዎችና ችግሮች ለመጠየቅ ለመወያየት በፍጹም አንደበታቸው እንደተዘጋና የደንፊዎችን ፕሮፓጋንዳ እንዲቀበሉ የተገደዱ መሆናቸውን ነው ።

የኢሠፓአኮን ድርጅታዊ መዋቅር ስንመለከት ደግሞ ድርጅቱ አንዳችም በጊዓዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተዋቀረ ባይሆን የጥቂት ቡዶች የበላይነት የሰፈነበት በተለይም የመንግሥቱ ኃይለማርያም የሥልጣን ሞኖፖል የተረጋገጠበት በሥልጣን ተዋረድ መሠረት አንዱ ለአንዱ የሚሰገድበት አዛዥና ታዛዥ የሰፈነበት ድርጅት ነው ። ይህም የሥልጣን ተዋረድና አዛዥ ታዛዥነት እንዲሁም ለድርጅቱ አባልነት የገዓጅ አባልነት በማዘዣ ደብዳቤ " ሰውን ሁሉ " መሰብሰብ ለኮሚሽኑ ለሚፈጠረው " የሠርቶ አደር ፓርቲ ፀረ–ዴሞክራሲነት በቂ ማስረጃ ነው ።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተዋቀረ ድርጅት ደግሞ ጥቂቶች የበላይነት እንዲጠበቁና ፈላጭ ቆራጭነታቸውን እንዲያነገሡ እንደሚረዳቸው የታወቀ ነው ። በፍርሐት የተዋጠውና የምሁር አልኸኝነት የማይሰማው የነውስ ከበርቴ መደብም የዚህ የዚህ የሥልጣን አጋዥና ተሸከሚ መሆኑ የታወቀ ነው ። በአለው ዕውቀቱ በአለመተማመኑ፣ የወደፊቱን የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታና አረማመድ አርቆ ለማየት በአለመቻሉ ዛሬ የሥልጣን ፍርፋሪ አገኘሁ ብሎ ለኢሠፓአኮ ኃላፊዎች በማጎብደዱ ከዚህም ከዚያም ያገኘትን ዕውቀት አጠናቅሮ በማቀረብ የዛሬው ገዥዎች አፈ–ቀላጤ የሆነው ይኸው የነውስ ከበርቴው አድርባይ ክፍል ነው ። በዚህ ዓይነት የሚመሠረተው ፓርቲ ደግሞ ጊዜያዊ መቻቻልን ይሰጠው እንደሆን እንጂ፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አይደለም ። በአሁኑ ወቅት አንዱ የሌላው ዕጣ እንዳይደርሰው ታማኝነቱን ለኢሠፓአኮና ለመንግሥቱ ኃይለማርያም ከያረጋጠ ለመኖር የሚፈልግ ነው ።

በሌላ በኩል በሚመሠረተው ፓርቲ ውስጥ የሚኖረው የሥልጣን ተዋረድ ሙሉ በሙሉ የተፈታ አይደለም ። በእርግጥ ሁሉም ታማኝነቱን ለመንግሥቱ ኃይለማርያም

ለማሳየት ተፍ ተፍ ቢልም፣ መዋቅሩ ቢለወጥ የትኛው ቦታ ይደርስን ይሆን እያለ መቀበዝበዙ አልቀረም ። ይሁንና፣ ያለው ሁኔታ እንደሚያረጋግጠው የመንግሥቱን ሥልጣን ምናጋል ለማረጋገጥ ሲባልና ሌላው " እንዳይቀጥና እንዳይገነፍል " ተቻችሎ ለመኖር ሲባል የኢሠፓአኮ የሥልጣን ተዋረድ ወደሚመሠረተው ፓርቲ መሸጋሸጉ አይቀርም ።

ይህ በፀረ— ዲሞክራሲ ፣ በመፈራረት ፣ አንዱ ለአንዱ በመስገዱና ለጊዜያዊ ጥቅም በመደለል የተመሠረተ አደራጅ ኮሚሽንና ከዚህ ውስጥ የሚፈልቀው ፓርቲ በምንም ዓይነት ሀገሪቱ ያለችበትን ማኀበራዊ ቀውስ ሊፈታው አይችልም ። ችግሩ እየተባባሰ እንዲሄድ የሚያደርገና የጥቂት ገለሰቦች መጠሪያና የስሸየት ኀብረትንና ገብረ አበሮቹን ጥቅም የሚያስጠብቅ ፓርቲ በመሆኑ ይህ ጠቅላላ ጉባዔ ይህንን ሁሉ ከመረመረና ካጠና በኋላ አገራችን ፣ አሁንም ወደፊትም በአዲስ ስም ለመግዛት የሚሞክረው የወታደሩ አምባገነን መንግሥት እንጂ ፣ ሌላ አለመሆኑን በመገንዘብ፣

ሀ/ የወታደሩ መንግሥት፣ በኢሠፓአኮና በኢሠፓ መሀከል አንዳችም ልዩነት እንደሌለና የዚህ የበላይ አዛዥ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም መሆኑን በመረዳት፣ ኢትዮጵያ ውስጥና ከኢትዮጵያ ውጪ የሚታገሉ ዲሞክራትና ተራማጅ ኃይሎች፣ እንዲሁም አገር ወዳጆች በዚህ የወታደር አምባገነን መንግሥት ላይ እንዲረባረቡ ይህ ጉባዔ ጥሪው ያቀርባል ።

ለ/ ከእንግዲህ አገሪቱን የሚገዛው የወታደር መንግሥት " ጊዜያዊ " ሳይሆን " ቋሚ " መሆኑን በመገንዘብ ይህ የሚመሠረተው የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ " የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች ፈጽሞ የማይወክል መሆኑን ጉባዔው በመረዳት ይህን የሚመሠረተውን ፓርቲ ፈጽሞ በማያወላውል መንገድ አቋሙ እስከሚፈቅድለት ድረስ ከሌሎች ፀረ—መንግሥት ኃይሎች ጋር እንዲሚቆምና እንደሚያጋልጠው ማኀበራችን እንደገና ቃሉን ያድሳል ።



ሐ/ የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች፣ አገር ወዳጆችና ተራማጆች ለአገር አቀፍ የኢትዮጵያ ወዝአደሮችና ጭቁን ሕዝቦች ፓርቲ መመሥረት አሳሳቢነቱን በመገንዘብ ለዚህ ሀቀኛ ፓርቲ መፈጠር የተቻላቸውን አስቸኳይ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጉባዔው ለሚመለከተው ኃይሎች ጥሪውን ያቀርባል ።

## ስለማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታ

የአንድ ሕዝብ የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታ የዚያው ሀገር የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተጻምዶ ነፀብራቅ ነው ። በአንድ አገር ውስጥ ሥርዓት ያለው አስተዳደር ከሌለ፣ ኢኮኖሚው ኪደቀቀና መልክ ባለው ሁኔታ ያልተዋቀረ ከሆነ፣ አብዛኛው ሕዝብ በዚህ የተበላሸ አስተዳደርና የተመሰቃቀለ ኢኮኖሚ ይመታል ። ወዝአደሩ በሥራው ቦታ አስፈላጊውን የመከላከያና ለአደጋ እንዳይጋለጥ የሚያደርጉትን ሕጋዊ እርምጃዎች ሊያገኝና ሊረጋገጥለት አይችልም ። ከሥራው ቦታ የሚፈናቀለው ወዝአደርና የሥራአጥ እንዲሆን የሚገደደው መብት ኖሮት የሥራ አጥ አበል ሊያገኝ አይችልም ። ትምሕርቱን እየጨረሰ የሚወጣው የሥራ መስክ በቀላሉ ሊያገኝ አይችልም ። እስኪያገኝም ድረስ መንግሥታዊ ድጋፍ አያገኝም ።

በእንደዚህ ዓይነት አስተዳደር ውስጥ ከሚሰቃዩት የሦስተኛው ዓለም ተብለው ከሚጠሩት ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያችን አንዷ ናት ። የኢትዮጵያ ወዝአደር ከየካቲት አብዮት ወዲህ አንዳንድ መብቶን የሚያስከብሩለትንና የሚያረጋግጡለትን ሕይወቶን በሥራ ቦታው የሚከላከሉትንና የሚጠብቁለትን መብቶች የተቀዳጀ ቢሆንም፣ ከአብዮቱ መቀልበስ ጋር እነዚህ መብቶች ተረግጠውበታል ። ከሥራ የሚባረረው ምንም ዓይነት የሥራ አጥ አበል አያገኝም ። ሲታመም የነጻ ሕክምና አያገኝም ። ይህ የመብትን ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን፣ በቂ የሥራ መስክ ለማግኘት ባለመቻሉ በሥራ አጥነት የሚሰቃየው፣ በሆነ ባልሆነው ሥራ የተሰማራውና በየበረንዳው ለብርድና ለውርጭ ተጋልጦ ካለምንም ድጋፍ የሚሰቃየው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ በውጭ ሀገር ታትመው የሚወጡ አስታትስቲክሶች ይገልጻሉ ።

የሴተኛ አዳሪዎቻችንም ሁኔታ የተመለከትን እንደሆነ ሁኔታው ከዚህ የተለየ አይደለም ። በቂ የሥራ መስክ ባለመከፈቱ፣ ይህ " ሶሻሊዝምን እገነባለሁ " የሚለው የወታደር መንግሥት፣ ዛሬ የሴተኛ አዳሪ ቁጥር ከየካቲት በፊት ከነበረው ሁኔታ በቁጥር ከፍ እንዲል አድርጓል ። የዚህ የሴተኛ አዳሪነት ሌላ መልኩ፣ ዛሬ በዙ ወጣት ኢትዮጵያውያት እህቶቻችን በተለይም በአስራ አራትና አስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ከቤተሰቦቻቸው ምንም ዓይነት እርዳታ ለማግኘት ስለማይችሉ፣ ወደዚህ አስከፊ ተግባር እንዲሠማሩ ተገደዋል ።

2613 353



የወንዱ ወጣት ወገናችን ሁኔታም ስንመለከት ሁኔታው እንደዚሁ አሳዛኝ ሆኖ እናገኘዋለን ። በትምህርት ቤት ጥበት ምክንያት፣ ትምህርቶን አጠናቅቆ በቀላሉ ሥራ ለማግኘት ባለመቻሉ ባልሆነ ቦታ እንዲሠማራ የተገደደው የወደፊቱ ኢትዮጵያ ገንቢ የሚሆነው ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ይህ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንደኛው ጎን ሲሆን፣ በሕክምና እጦትና፣ በሀኪም ቤት ጥበት ለአምስተ ለስድስት እየተጣበበ የሚኖረው፣ ኑሮውን በሆቴል ቤት እንዲያደርግ የተገደደው ምሁር ቁጥር እያደገና የሳይኮሎጂካል ውድቀት ውስጥ እየተዘፈቀ መጥቷል ። ይህ ሁኔታ የቤተሰብን የባሕል ሁኔታ እንደሚያበላሽና በሀገሪቱ የባሕል ዕድገት እረማመድ ላይ ከፍተኛ እሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ገልጽ ነው ።

ይህ 24ኛው ጠ/ጉባዔ ይህን ሁኔታ በሰፊው ከመረመረና ካጠና በኋላ፣ ይህ ለጥንቀሳት የሚዘገንን የሀገራችን ሁኔታ ሊሻሻል የሚችለውና መሠረታዊ የሆነ ለውጥ የሚያገኘው የዛሬው አገዛዝ ሲገረሰስ፣ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲቋቋምና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ተቀጭ ሰፊውን ሕዝብ በሚጠቅምና ኑሮውን ሊያሻሽል በሚችል መንገድ ሲዋቀር ብቻ ነው ብሎ ያምናል ።

## መኢሶን

ማህበራችን፣ ለመላው የኢትዮጵያ ሶሻሊስት እንቅስቃሴ ከዚሁ ቀደም በተደጋጋሚ የፖለቲካ ድጋፍ እንደሰጠው ይታወቃል ፡፡ ዛሬም ይህ ድርጅት ለኢትዮጵያ ህዝቦች የገባውን እውነተኛ የነፃነት፣ የዲሞክራሲ፣ የብሔር/ብሔረሰቦች መብትና እኩልነት፣ የኢኮኖሚ ብልጽግናና ሰላም፣ቃል ኪዳን ቢያቀፍ የሚታገል በመሆኑ ይህ ጉባዔ ይህን ሁኔታ ከመረመረ በኋላ ለድርጅቱ አብዮታዊ ድጋፉን እንደገና ያድባል ፡፡

የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት እንቅስቃሴ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታገል ድርጅት እንደመሆኑ መጠን፣ዛሬ ሀገራችን ውስጥ ለሰፈነው የፀረ–ዲሞክራሲ አገዛዝ መደምሰስ ፣ ለብሔራዊ ነፃነታችን መታደስ ከምንግዜውም የበለጠ ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት ፡፡ በመሆኑም የተሰበጣጠሩትን ኃይሎች የመሰብሰብና የማደራጀት፣ ከሌሎች ከተደራጁ የብሔርብሔ ረሰብ እንቅስቃሴዎች ጋር የጋራ ግምባር ለመመስረት በሚያደርገው ትግሉ እንዲገፋበት ይህ ጉባዔ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርብለታል ፡፡ በዚህም ከጎኑ ቆሞ ይታገላል ፡፡